ይፈልጋል። በተርድሚል ኢንስቲቱት ያለነዉ ሁሉ እግዚአብሔር በዚህ ሂደት ዉስጥ በህይወታቹ የሚያደርገዉን ለማየት እና ለመስማት ጓጉተናል።

## አሰልጣኝ ምን ማለት ነዉ?

ዓላማችን ሁልም ተማሪ አንድ በአንድ ቢሆንም በትናንሽ ቡድን ዉስጥ በአሰልጣኝ እንዲመራ ነዉ። የአሰልጣኙ ዋና ስራ ሳምንታዊ የዉይይት ጊዜዉን መምራት እና የአንስቲቱቱን በጅ/አርማ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሟላት እንደትችሉ ማገዝ ነዉ። አሰልጣኞች የተማሪዎችን ስራ መከታተል እና ሰርተፊኬት/ዲፕሎማ ለማግኘት ማሟላት ያለባቸዉን ሁሉ ማሟላታቸዉን ማረጋገጥ አለበት።

## አሰልጣኝ እንዴት ይገኛል?

አሰልጣኝ ሊሆን የሚችል ሰዉ ጋር ተገናኝተዉ ይሆናል። ከቤተክርስትያን ወይም ከማህበረሰቡ ዉስጥ እሄንን የስራ ድርሻ መዉሰድ የሚችል ሰዉ አግኝተዉ ይሆናል። እሄ ሰዉ ግን ማቴሪያሉን ሁሉ አስቀድሞ እንዲያይ እንጠይቃለን። በተርድሚል ኢንስቲቱት ኔትወርክ በኩል አሰልጣኝ እንዲያገኙ ልንረዳዎ እንችላለን። በ institute.thirdmill.org አግኙን። ድንገት አሰልጣኝ ማግኘት ካልተቻለ ተቆጣጣሪ በሌለው መልክ ሊሰጥ ይችላል እሄንን ግን አንመክርም።

## የመማሪያ ብድን/ማህበረሰብ

በተርድሚል ኢንስቲቱት በትንሽ ቡድን ዉስጥ እንዲሰራ ታስቦ ነዉ የተሰራው። የመማሪያ ቡድኑ ተማሪዎችን እና አሰልጣኞችን ይይዛል። አንድ ተማሪ እና አሰልጣኝ ሊሆን ይችላል ወይም የተወሰኑ ተማሪዎች ከአንድ አሰልጣኝ ጋር ሊሆን ይችላል። ቡድኑ ከ4-10 ሰው እንዲይዝ እንመክራለን።ከቡድናቹ ጋር በየጊዜው በመገኛኘት ብዙ ትማራላቹ። በእነዚህ ዉይይት በኩል የተማራቹትን ቅርፅ ታስይዛላቹ ወደ ሚኒስትሪያቹ እና ከእግዝአብሔር ጋር ወዳላቹ ግንኙነት እንዴት ማምጣት እንደምትችሉ ትማራላቹ።

በሳምንት 3-5 ሰዓት በራሳቹ እንደምታጠኑ እና በቡድን ደሞ 1-1፡30 እንደምታጠኑ እናስባለን። አሰልጣኙ በሳምንት አንድ ጊዜ እንድትገናኙየ ከወሰነ ሰርተፊኬቶቹ 4-5 ኮርሶች ይይዛሉ። ኮርሶቹ ደሞ ከ7-11 ሳምንት ይወስዳሉ።

3 ሰርተፊኬት = 1 ዲፕሎማ

ተርድሚል ኢንስቲቱት 3 የተለያዩ ሰርተፊኬቶችን ይሰጣል። ሶስቱም ከተጠናቀቁ ደሞ የኢንስቲቱቱን ዲፕሎማ በክርስትና ሚኒስትሪ ይሰጣል። የመጀመሪያው ሰርተፊኬት የመሰረት / ፋዉንዴሽን ሰርተፊኬት ይባላል። እሄ 4 ኮርስ የሚይዘው ሰርተፊኬት በመፅሀፍ ቅዱስ እና ስነመለኮት ጥሩ መሰረት ይጥላል። ቡድኖች ከዚህ መሰረት መጀመር ይኖርባቸዋል። እሄንን ካጠናቀቁ በዉሀላ ቡድኖች ወደ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናቶች ሰርተፊኬት፣ ስነመለኮት ጥናቶች ሰርተፊኬት ወይም ወደ ሁለቱም ጥናት መቀጠል ይችላሉ። በኮርሶች መሀል ዕረፍት ከተወሰደ አንድ ሰርተፊኬት አንድ ዓመት አካባቢ እንዲወስድ ተደርጎ ነዉ የተሰራዉ። እንደ ቡድናቹ ዉሳኔ ግን ከዚህ ጊዜ ባነሰ ወይም በበዛ ጊዜ ሊጨረስ ይችላል።

